يقين
YAQEEN
مكتب الدعوة والإرشاد بالمعذر وأم الحمام



باللغة الإثيوبية (أمهري)

# هل الموسيقى والغناء لم تحرم في الشريعة ؟؟؟

# እውን ሙዚቃና ዘፈን በኢስላም አልተከለከለምን ???


አዘጋጅ፡ዳዒ/ ሙሀመድ ሀሰን ማሚ

إعداد : الداعية / محمد حسن مامي

بسم الله الرحمن الرحيم

الحمد لله رب العالمين والصلاة والسلام على رسول الله . أما بعد :-

እንደሚታወቀው ኢስላም ሰፊና ጥልቅ አስተምህሮቶች፣ ረቂቅ መመሪያዎችና ድንጋጌዎች አሉት፡፡ ሁሉንም የህይወት ዘርፍ ዳስሷል። ሳያስተምረን ያለፈው የህይወት ጉዳይ የለም። በተለያየ መልክና ዘዴ እያንዳንዱን የህይወት ክፍል በመዳሰስም ወደር የሌለው ሃይማኖት ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ ይህንንም እውነታ የማንኛውም አማኝ ልቦናና ህሊና ያውቀዋል፡፡

ሆኖም በኢስላም ድንጋጌ እና መመሪያ ብይን በየጊዜው እና በየወቅቱ የተለያዩ ብዥታዎችና ውዥንብሮችን የሚፈጥሩ ሰዎች አልጠፉም፣ አሉም፣ ይኖራሉም፡፡ በየጊዜው ብቅ ጥልቅ ከሚሉ በርካታ ውዥንብሮች መካከል የሙዚቃን ላይ የተመለከተው ይጠቀሳል። የራሳቸውን ግንዛቤ ለማስፋፋት ሲፈልጉ፣ ኢስላም ስለዘፈንም ይሁን ስለሙዚቃ ክልክልነት የተናገረው ነገር የለም፡፡ ክልክል ለመሆኑ የቀረቡ መረጃዎችንም የወደቁና ተቀባይነት የሌላቸው እንደሆኑ፣ ሲጠኑ በሁለት እግር መቆም የማይችሉ እንደሆኑ አድርገው በማቅረብ የሚነዙት ብዥታ ተራ አሉባልታ እንደሆነ በዚህ መልእክቴ ለማሳየት እሞክራለሁ፡፡



አላህ ስራችንን ሁሉ በኢኽላስ የተፈፀመ እንዲያደርገው እለምነዋለሁ። እገዛንም ከእርሱ ብቻ እጠይቃለሁ፡፡

** ዘፈንና ሙዚቃ በኢስላም የተከለከለ መሆኑን ከተለያዩ ኢስላማዊ መረጃዎች ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

1ኛ- ከቁርኣን ፤
2ኛ- ከሐዲስ ፤
3ኛ- ከሰሃቦች አንደበት ፤
4ኛ- ከታቢዒዮች አንደበት ፤
5ኛ- ከአራቱ መዝሃቦች አቋም እና
6ኛ - ከኢጅማዕ አሰለፍ (ከቀደምት ትውልዶች የጋራ አቋም) ።

## 1ኛ - ከቁርኣን፦

❶ በሱረቱል ሉቅማን ቁጥር 6 አላህ ( ) እንዲህ ብሏል :-

﴿وَمِنَ النَّاسِ مَن يَشْتَرِي لَهْوَ الْحَدِيثِ لِيُضِلَّ عَن سَبِيلِ اللَّهِ بِغَيْرِ عِلْمٍ وَيَتَّخِذَهَا هُزُوًا أُولَٰئِكَ لَهُمْ عَذَابٌ مُّهِينٌ ﴿٦﴾﴾ لقمان

“ከሰዎችም ያለ እውቀት ሆኖ ከአላህ መንገድ ሊያሳስትና ማላገጫ አድርጎ ሊይዝ ለህወል ሀዲስ (አታላይ ወሬን) የሚገዛ አለ፣ እነዚያ እነሱ አዋራጅ ቅጣት አላቸው፡፡”

በእዚህ አንቀፅ ውስጥ “ለህወል ሀዲስ” (አታላይ ወሬ) ተብሎ የተሰየመውና ቅጣቱም አወራጅ ተብሎ የተዛተበት ምን ይሆን? መልሱን ከሰሃቦች አንደበት መረዳት

ይቻላል።

ሀ. ዐብድላህ ኢብኑ መስዑድ (አላህ መልካም ስራውን ይውደድለት) /ስለ ቁርኣን ጥልቅ እውቀት ካላቸው ስመ-ጥር ባልደረቦች አንዱ ነው።/ ስለ "ለህወል ሀዲስ" (አታላይ ወሬ) ሲጠየቅ ሶስት ጊዜ በመማል "ዘፈን ነው ፡ ዘፈን ነው ፡ ዘፈን ነው" ብሎ መመለሱን ኢብኑ አቡ ሸይባ፣ ኢብኑ ጀሪር፣ አልሃኪም፣ አልበይሀቂ እና ኢብኑልጀውዚ ዘግበዋል ።

ለ. ዐብደላህ ኢብኑ ዐባስ /አላህ መልካም ስራውን ይውደድለት/፡/የሙስሊሙ ማህበረሰብ አዋቂ፣በቁርኣን ማብራሪያ ላቅ ያለ እውቀት ያለውና የአላህ መልእክተኛም "አላህ ሆይ ሃይማኖቱን አስገንዝበው የቁርኣንንም ማብራሪያ አሳውቀው።" ብለው ዱዓእ ያደረጉለት ስመ- ጥር ሰሃባ ነው።/ ስለ ለህወል ሀዲስ" (አታላይ ወሬ) "ዘፈንና መሰሎቹ ናቸው" ማለቱን ኢብኑ አቡ ሸይባህ ፣ (ቡኻሪ፣ ኢብኑ ጀሪር፣ አልበይሀቂ፣ እና ኢብኑ ጀውዚ ዘግበዋል።)

ሐ. ዐብደላህ ኢብኑ ዑመር (የመዲና ሙፍቲና የፊቂህ ምሁር ) ለህወል ሀዲስን በማስመልከት "እርሱም ዘፈን ነው" በማለት አብራርቶታል።

መ. ጃቢር ኢብኑ ዐብደላህ (ከዐብደላህ ኢብኑ ዑመር ቀጥሎ የመዲና ሰዎች ፈቂህ / ምሁር እንዲሁም ሙፍቲ የነበረው) "ዘፈንና ማዳመጡ ነው" ማለቱን ኢብኑ ጀሪር ዘግቧል።

✓ እነዚህ ታላላቅና ስመጥር ሰሃቦች ይህን አንቀፅ በተመለከተ (ዘፈን) መሆኑን አረጋግጠዋል፣ የሰሃቦችም ማብራሪያ ማስረጃ ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም፣ ይህንም ማብራሪያ የተቃረነ አንድም ሰሃባ የለም።

** ሰሃቦችም እንዲህ ብለው እንደተረጐሙት ሁሉ ታቢዒዮችም በተመሳሳይ መልኩ አብራርተውታል፡ ፡ እንደሚከተለውም ዝርዝራቸውን እጠቅሳለሁ።

1. ሙጃሂድ ኢብኑ ጃብር
2. ዒክሪማህ
3. መክሁል
4. ኢብራሂም አል-ነኸዒ
5. ዐጣእ
6. ሰዒድ ኢብኑ ጁበይር
7. ሐሰን አልበስሪ
8. ቀታዳህ ኢብኑ ደዓማ
9. መይሙን ኢብኑ ሚህራን
10. ሀቢብ ኢብኑ አቢሳቢት
11. ዐምር ኢብኑ ሹዓይብ
12. ዐብዱልመሊክ ኢብኑ ጁረይጅ
13. ሰዒድ ኢብኑልሙሰይብ ናቸው ፡፡



❷ ሱረቱ አነጅም ቁጥር 59 – 61

﴿أَفَمِنْ هَٰذَا الْحَدِيثِ تَعْجَبُونَ ۝٥٩ وَتَضْحَكُونَ
وَلَا تَبْكُونَ ۝٦٠﴾ النجم

“በዚህ ንግግር ትደነቃላችሁን?!
ትስቃላችሁምን? አታለቅሱምን? እናንተም
ዘንጊዎች ናችሁ:: ”

ይህንም አንቀፅ በማስመልከት ዘንጊዎች ተብሎ የተተረጐመው ቃል በአረበኛው “ሳሚዱን” የሚለው ቃል ሲሆን ትርጉሙን በተመለከተ የየመን ቋንቋ እንደሆነ በመጥቀስ “ዘፈን ” እንደሆነ ዐብደላህ ኢብኑ ዐባስ ፣ ሙጃሂድ፣ ዒክሪመህ ና አደሃክ ገልፀዋል ::

❸ ሱረቱል ኢስራእ ቁጥር 64

﴿وَاسْتَفْزِزْ مَنِ اسْتَطَعْتَ مِنْهُم بِصَوْتِكَ وَأَجْلِبْ عَلَيْهِم بِخَيْلِكَ وَرَجِلِكَ وَشَارِكْهُمْ فِي الْأَمْوَالِ وَالْأَوْلَادِ وَعِدْهُمْ وَمَا يَعِدُهُمُ الشَّيْطَانُ إِلَّا غُرُورًا ﴿٦٤﴾﴾ الإسراء



“ከእነሱ የቻልከውንም ሰው በድምጽህ አታል፣በእነሱም ላይ በፈረሰኞችህ፣ በእግረኞችህም ለልብ(ጋልብባቸው): : በገንዘቦቻቸውም፣ በልጆቻቸውም ተጋራቸው፣ ተስፋ ቃልም ግባላቸው: : ሰይጣንም ማታለልን እንጂ ተስፋ ቃልን አይገባላቸውም:: ”

- ሙጃሂድ ኢብኑ ጀብር (የዐብደላህ ኢብኑ ዓባስ ታላቅ ተማሪ) የኢብሊስ ድምፅ ምንነትን ሲገልፁ እንዲህ ነበር ያሉት :- “እርሱም ጊናእ (ዘፈን)፣ የሙዚቃ መሳሪያ፣ ላግጣና ከንቱ ነገር ነው::”
- አድሃክም “ የዘፋኝ (የሙዚቃ መሳሪያ) ድምፅ ነው” ብለዋል ።
- ኢብኑል ቀይምም እንዲህ በማለት የዘፈንን ምንነት ይገልፃሉ :- “ዘፈን ከታላላቅ የሰይጣን ድምፆችና ነፍስን የሚያስበረግግበት፣ የሚረብሽበት እና ሰላም የሚነሳበት ለመሆኑ አያጠራጥርም ። የነፍስ መረጋጋት ፣ ሰላም የምትጋኝበት እና ወደ ጌታዋ እንድትመለስ የሚያደርገውን ቁርኣንን የሚፃረር ነው ።”

❹ ሱረቱል ሀጅ ቁጥር 30

﴿ذَٰلِكَ وَمَن يُعَظِّمْ حُرُمَاتِ اللَّـهِ فَهُوَ خَيْرٌ لَّهُ عِندَ رَبِّهِ وَأُحِلَّتْ لَكُمُ الْأَنْعَامُ إِلَّا مَا يُتْلَىٰ عَلَيْكُمْ فَاجْتَنِبُوا الرِّجْسَ مِنَ الْأَوْثَانِ وَاجْتَنِبُوا قَوْلَ الزُّورِ ﴿٣٠﴾﴾ الحج


“ሐሰትንም ቃል ራቁ”

ሙሐመድ ኢብኑል ሐነፍያህ “የሐሰት ቃል ” ተብሎ የተተረጐመውን “ቀውለ ዝዙር” ን ሲያብራሩ “እርሱ ዘፈን ነው” በማለት ገልፀዋል::

❺ ሱረቱል አንፋል ቁጥር 35

﴿وَمَا كَانَ صَلَاتُهُمْ عِندَ الْبَيْتِ إِلَّا مُكَاءً وَتَصْدِيَةً فَذُوقُوا الْعَذَابَ بِمَا كُنتُمْ تَكْفُرُونَ ﴿٣٥﴾﴾ الأنفال

“በቤቱ(በከዕባ)ዘንድም ስግደታቸው ማፏጨትና ማጨብጨብ እንጂ ሌላ አልነበረም፡፡”



“ማፏጨትና ማጨብጨብ” የሚለው ትርጉም (ሙካአን ወተስዲየተን) የሚለው የዐረበኛ ቃል ትርጉም ሲሆን መልዕክቱን በተመለከተ ዘፈንን ለማለት እንደተፈለገ በርካታ የቁርአን ሙፈሲሮች (ተንታኞች) ገልፀዋል፡፡ ከእነዚህም ግንባር ቀደም ሙፈሲሮች(ተንታኞች) ዐብደላህ ኢብኑ ዐባስ፣ ዐብደላህ ኢብኑ ዑመር፣ ኢብኑ ጁበይር ፣ ቀታዳህ እና የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡
? የዘፈንን ፍርድ የሚገልፁና የሚያብራሩ የቁርአን አንቀፆችና ማብራሪያቸውን እንደተመለከትነው ዘፈንና ሙዚቃን አበክረው እንዳወገዙና እንደተቹ ነው ፡፡

☙ በመቀጠልም ወደ ሁለተኛው መረጃችን ሐዲስ ስንሻገር ፡-

## 2ኛ . ከሀዲስ፡-

2.1- ኢማሙል ቡኻሪ አቡ ማሊክ አል አሽዓሪን ዋቢ በማድረግ እንደዘገቡት የአላህ መልእክተኛ(ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ) ፡-

“ليكونن من أمتي أقوام يستحلون الحر والحرير والخمر ”

“ከእኔ ዑመት(ህዝቦች) መካከል፣ ዝሙትን፣ ሐርን ፣ አስካሪ መጠጥን እና ሙዚቃን ልክ እንደሐላል(እንደተፈቀደ )አድርገው የሚጠቀሙ ይመጣሉ” ብለዋል።
ይህ ሐዲስ ሙዚቃንና መሰሎቹ ሐራም እንደሆነ ያመለክታል ይሄውም “እንደሐላል(እንደተፈቀደ ) ” የሚለው ቃል ክልክል ሆኖ እያለ እነሱ ግን እንደሐላል(እንደተፈቀደ) አድርገው መጠቀማቸውና መያዛቸው የተወገዘ ተግባር እንደሆነ በግልጽ ያስረዳል ፡፡

2.2- ዐብዱራህማን ኢብኑ ዓውፍ እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ (ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ) ፡-

«وَلَكِنْ نَهَيْتُ عَنْ صَوْتَيْنِ أَحْمَقَيْنِ فَاجِرَيْنِ : صَوْتِ نَغْمَةٍ لَهْوٍ وَلَعِبٍ وَمَزَامِيرِ الشَّيْطَانِ ،»

“የከለከልኩት ሁለት ጠማማና ቂል የሆኑ ድምፆችን ነው፣ የደስታ ጊዜ ጩኸት ይሄውም ለህው (ላግጣ) (ጩኸቶች) ለዒብ (ጫዎታ) እና የሰይጣን መሰንቆን ፣ የአደጋ ጊዜ ጩኸት (ድምፅ) ማለትም “ፊትን መቧጠጥ፣ ልብስን መተርተርና የሰይጣን ድምፅ ናቸው” (ቲርሚዚ፣ አልሃኪም፣ ኢብኑ ሰዕድና ሌሎችም ዘግበውታል )።

በዚህ ሐዲስ ላይ የአላህ መልእክተኛ (ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ) የሙዚቃ መሳሪያ “የሰይጣን” ብለው መግለፃቸው ከዚያም በፊት “የከለከልኩት” ማለታቸው ዘፈን የተከለከለ እንዲሁም የሰይጣን ተግባር መሆኑን በግልፅ የሚያስረዳን ማስረጃ ነው፡፡



2.3- ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያህ ይህን ሐዲስ በማስመልከት እንዲህ ብለዋል :- “ይህ ሐዲስ ዘፈን ሐራም ነው ተብሎ ለማስረጃነት ከሚቀርቡት ሃዲሶች ሁሉ በጣም ምርጡ ነው፡፡” (አልኢስቲቃማህ)

2.4- ኢማሙ ቲርሚዚ ዒምራን ኢብኑ ሁሰይንን ዋቢ በማድረግ ከነብዩ (ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ) እንዳስተላለፉት :-

عن عمران بن الحصين أن رسول الله ﷺ قال : في هذه الأمة خسف ومسخ وقذف، فقال رجل من المسلمين : يارسول الله ومتى ذلك ؟ قال : إذا ظهرت القينات والمعازف وشربت الخمور . رواه الترمذي وصححه الألباني .

“በእዚህ ህዝብ ላይ ምድር ተከፍታ መሰጠም፣ የመልክ መቀየርና በድንጋይ መቀጥቀጥ ይከሰታል” ሲሉ ከሙስሊሞች አንዱ “መቼ ነው?” ብሎ ሲጠይቅ መልእክተኛውም “ዘፋኝ ሴቶችና ሙዚቃ ይፋ ሲወጡ እንዲሁም አስካሪ መጠጥ በግልፅ የተጠጣ ጊዜ ነው፡፡” በማለት መለሱለት ፡፡

ይህ ሀዲስ ምንም ዓይነት ተጨማሪ ማብራሪያ አያስፈልገውም ፡፡ማስረጃነቱ እጅግ ግልፅ ነው ፡፡

2.5- አልኢማሙ ሙስሊም አቡሁረይራህን ዋቢ በማድረግ የአላህ መልእክተኛ (ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ) እንዲህ ማለታቸውን ዘግበዋል :-

“ደውል የሰይጣን መሰንቆ ነው፡፡”

2.6- አቡ ዑበይድ፣ ኸላል፣ በይሃቂና በገዊ አቡሁረይራን ዋቢ በማድረግ የአላህ መልዕክተኛ (ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ) :- “በዘፈን የሚገኘን ገቢ ከልክለዋል፡፡”



እነዚህንና መሰል ሀዲሶችንም መጥቀስ ይቻላል፡፡ ግና አስተዋይ እና ንፁህ አእምሮ ያለው በርካታ ሳይሆን አንድና ግልፅ ማስረጃ ከመጣለት ይበቃዋል፡፡ ቢሆንም ነገሩ አላህ :-

﴿إِذْ أَنتُم بِالْعُدْوَةِ الدُّنْيَا وَهُم بِالْعُدْوَةِ الْقُصْوَىٰ وَالرَّكْبُ أَسْفَلَ مِنكُمْ وَلَوْ تَوَاعَدتُّمْ لَاخْتَلَفْتُمْ فِي الْمِيعَادِ وَلَـٰكِن لِّيَقْضِيَ اللَّـهُ أَمْرًا كَانَ مَفْعُولًا لِّيَهْلِكَ مَنْ هَلَكَ عَن بَيِّنَةٍ وَيَحْيَىٰ مَنْ حَيَّ عَن بَيِّنَةٍ وَإِنَّ اللَّـهَ لَسَمِيعٌ عَلِيمٌ ﴿٤٢﴾﴾ الحج

“የጠፋ ሰው መረጃ ከመጣለት በኋላ

እንዲጠፋ፣ ሕያው የሚሆን ሰው መረጃ ከመጣለት በኋላ ሕያው እንዲሆን”

እንዳለው ስለሆነ ነው፡፡

## 3ኛ. ከሰሃቦች ንግግር

በዘፈን ላይ ከቁርኣንና ከሐዲስ መመሪያ ሊወጡ ስለማይፈልጉ ፡ ልክ ቁርኣንና ሐዲስ የሰጣቸውን መልእክት የሚያረጋግጥ ንግግርና አቋም ነበራቸው። ለማንኛውም የእነርሱንም አቋም መመልከቱ ያስፈልጋል፡ ፡



3.1- አቡበክር አሲዲቅ (አላህ መልካም ስራውን ይውደድለት ) ሁለት ህፃን ሴት ልጆች ድቤ እየመቱ ሲዘፍኑ ተመለከተና ከለከላቸው እንዲህም አለ ፡- “የሸይጣን ዝማሬ (ማሲንቆ) ነው፡፡” የአላህ መልእክተኛም (ሰላላሁ ዐለይሂ ወሰለም ) ይህን ተመልክተው አልተቃወሙትም ፡፡ (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)።

3.2- ዑስማን ኢብኑ ዓፋን (አላህ መልካም ስራውን ይውደድለት) ከዚህ ቀደም በዚህ ወንጀል ላይ እንዳልወደቀ የአላህን ፀጋ ሲያወሳ እንዲህ በማለት ነበር ፡- “አልዘፈንኩም አልተመኘሁምም ” (ኢብኑ ዓሲምና ጠበሪ ዘግበውታል)።

3.2- ዐብደላህ ኢብኑ መስዑድ (አላህ መልካም ስራውን ይውደድለት) “ማንኛውም ግለሰብ ሲጋልብ የአላህን ስም ካላወሳ ሰይጣን አብሮት ይፈናጠጥና እንዲህም ይለዋል “ዝፈን” ። የማይችል ከሆነ ደግሞ “ተመኝ” ይለዋል፡፡ ማለቱን (ዐብዱረዛቅ፣ ጠበራኒና ኢብኑ አቢ አዱንያ ዘግበውታል፡፡)

3.4- በድጋሚም እንዲህ ብሏል ፡- “ውሃ አዝእርትን (አትክልትን)እንደሚያበቅል ሁሉ ዘፈን ልብ ውስጥ ኒፋቅን(አስመሳይነትን) ያበቅላል፣ ውሃ በቆልትን እንደሚያበቅልም ሁሉ ዚክር (አላህን ማውሳት እና ማወደስ ) ደግሞ ኢማንን በልብ ውስጥ ያበቅላል” (ኢብኑ አቢ ዱንያና በይሀቂ ዘግበውታል፡፡)

3.5- እንዲህም ብሏል፡- “ዘፈን የዝሙት ማጪያ(መንደደሪያ) ነው፡፡”

3.6- አነስም (አላህ መልካም ስራውን ይውደድለት) እንዲህ ብሏል ፡- “(ከገቢ ምንጭ) ሁሉ መጥፎው የዘፋኝ የገቢ ምንጭ ነው፡፡”

3.7- ዐብደላህ ኢብኑ ዑመር (አላህ መልካም ስራውን ይውደድለት) ሐጅ ወይም ዑምራ ለማድረግ የነየቱ (ያሰቡ) ሰዎች አጠገብ ሲያልፍ ከመካከላቸው የሚዘፍን ሰው ሰማ እንዲህም በማለት ዱዓእ አደረገባቸው “አላህ ጥሪያችሁን አይቀበል ፡፡ጥሪያችሁን አይቀበል፡፡”

3.8- አሁንም በድጋሚ አንዲት ህፃን ልጅ ስትዘፍን ተመለከተና እንዲህ አለ “ሰይጣን ማንንም ንቆ ቢተው (ቢያልፍ) ኖሮ ይህችን ህፃን ልጅ ይተው (ያልፍ) ነበር፡፡”

3.9- እናታችን ዓኢሻህ (አላህ መልካም ስራዋን ይውደድላት) አንድን ሰውዬ ቤት

ውስጥ እየዘፈነና ጭንቅላቱን እየወዘወዘ አየችውና "ኡፍ ሰይጣን ነው አስወጡት አስወጡት" አለች ከዚያም ከቤት አስወጡት።

3.10- ዐብደላህ ኢብኑ ዐባስ (አላህ መልካም ስራውን ይውደድለት) "ከበሮ ሐራም ነው፣ ሙዚቃም ሐራም ነው ..."

## 4ኛ . ከታቢዒዮች

ታቢዒዮችም በበኩላቸው ሐራምነቱን ካለምንም ልዩነትና ውዝግብ በጋራ አፅደቀዋል። ንግግራቸውና አቋማቸውንም እንደሚከተለው እንገልፃለን፡፡

4.1- ወኪዕ ኢብኑል ጀራህ እንዲህ ብለዋል ፡- "ኢብኑ ዑመር እንዳደረጉት ጥሩንባውን (ዋሽንቱን) ቀማውና ጭንቅላቱ ላይ ሰበረው"።



4.2- ዘይኑል ዓቢዲን ፡- "በርበጥ" (የሙዚቃ መሳሪያ ነው) ያለበት ማህበረሰብ ምንም አልተባረከም" ይል ነበር ፡፡

4.3- ራፊዕ ኢብኑ ሐፍስ አልመደኒ ፡- "አራት ዓይነት ሰዎችን አላህ የትንሳኤ ዕለት በእዝነት ዐይን አይመለከታቸውም፡- ደጋሚ፣ አስለቃሽ፣ ዘፋኝ እና ባሏን ያታለለች" ማለታቸውን ኢብኑ አቢ አዱንያ ዘግበዋል።

4.4- አንድ ሰውዬ አል ቃሲም ኢብኑ መሐመድን ስለዘፈን እንዲህ በማለት ጠየቃቸው ፡- "ሐራም ነውን ? " ለጠያቂውም "አላህ እውነትን ከውሸት ሲለይ ከየትኛው የሚያደርገው (የሚመድበው) ይመስልሃል?" በማለት ጠየቁት እርሱም "ከውሸት ጋር " ሲላቸው እሳቸውም "እንደዚያው ነው" በማለት መልሱን ሰጡት" (አልበይሀቂ ዘግበውታል)።

4.5- ሰዒድ ኢብኑ ልሙሰይብም "በእርግጥም ዘፈንን እጠላለሁ" ማለታቸውን ዐብዱረዛቅ ዘግቧል።

4.6- አሽዕቢ እንዲህ ማለታቸው ተዘግቧል ፡- "ዘፋኝና የሚዘፈንለት ተረግመዋል፡፡"

4.7- አልፉደይል ኢብኑ ዒያድ ፡- "ዘፈን የዝሙት መሸጋገሪያ(መሰላል) ነው፡፡" ብለዋል

4.8- መክሁል እንዲህ ብለዋል ፡- "ዘፋኝ(አዝማሪ) ቤቱ እያለች የሞት ሰው ላይ አንሰግድበትም፡፡"

4.9- ኢብራሂም ኢብኑ ልሙንዚር እንዲህ ተጠየቁ ፡- "ስለዘፈን(ዘፈንን) ታግራራላችሁ?" እንዲህ በማለት መልስ ሰጡ "በአላህ እንጠበቃለን! እኛ ዘንድ አመፀኞች እንጂ አያደርጉትም።"

4.10- አደሃክ ፡- "ዘፈን ልብን የሚያበላሽ ጌታን የሚያስቆጣ ነው። "

4.11- አልሃሪስ አልሙሃሲቢ፡- "ዘፈን እንደ በክት (የሞተ እንስሳ) ሐራም ነው፡፡"

## 5ኛ. የአራቱ መዝሃብ መሪዎች ስለ ዘፈን፦

5.1- አልኢማሙ አቡ ሐኒፋ ዘፈንን አጥብቀው ከሚከለክሉት ነበሩ ፣ ማዳመጡንም እንደወንጀል ይቆጥሩት ነበር። የእሳቸው ባልደረቦችም (ተከታዮችም) የሙዚቃ መሳሪያን ማድመጥ ሐራም ነው ይሉ ነበር፡፡ በተጨማሪም "ሙዚቃን ማድመጥ ወንጀል ነው ፣የሚዘፈንበት ቦታ መቀመጥ አመፅ ነው፣ በዘፈን መርካትና መደሰት ክህደት ነው፡፡" እስከማለት ደርሰዋል።

5.2- አልኢማሙ ማሊክን ፦ የመዲና ሰዎች ዘንድ የተፈቀደ ዘፈን አለ እንዴ? ብለው ሲጠይቋቸው "እኛ ዘንድ ይህንን ተግባር የሚፈፅሙት አመፀኞች (ጋጠ-ወጦች) ናቸው" በማለት ነበር መልስ የሰጡት።



5.3- አልኢማሙ አሻፊዒይም ዘፋኝ ወንድና ሴትን በማስመልከት "የአንዳቸውም የምስክርነት ቃል ተቀባይነት የለውም ፣ ይህንም የፈፀመ ቂልና ክብረ-ቢስ ይሆናል፡፡" ብለዋል "ይህም ግዴለሽነት ነው ።"

በተጨማሪም "ዒራቅ ውስጥ ተግቢር (ድቤ እየመቱ በዜማ ዚክር ማድረግ) የሚባል ነገር መናፍቃን ሰዎችን ከቁርአን ለመግታት የፈጠሩት አዲስ ነገር ጥዬ መጥቻለሁ፡፡" ብለዋል ።

5.4- አልኢማሙ አህመድ ፦ "የሙዚቃ መሳሪያ ክራር፣ ከበሮ፣ ዋንሽትና መሰሎቹ ሐራም ነው፡፡"
አንድ ጊዜ አንድ ሰው ጀናዛ (አስከሬን) ለማጠብ ጠራኝና የከበሮ ድምፅ ሰማሁ" ብሎ ሲጠይቃቸው ፣ እሳቸውም "ከበሮውን መስበር ከቻልክ ስበረው ካልሆነ ግን ጥለህ ውጣ" በማለት መልስ ሰጡት ።

## 6ኛ. ኢጅማዑ አሰለፍ

ኢጅማዕ ሲባል በአንድነት ካለምንም ልዩነትና ውዝግብ በአንድ ድምፅ የፀደቀ ስምምነት ማለት ነው፡፡
በአንድ ድምፅ መስማማታቸውን የሚያመለክቱ ነገሮች ፦

ሀ. እስካሁን እንደተመለከትነው ከሰሃቦችም ይሁን ከታቢዒዮች ይህን አቋም በትክክለኛ ዘገባ ተቃውሞ የመጣ አለመኖሩና ይህንም ጉዳይ የውዝግብ ጉዳይ አድርገው እንዳልወሰዱት የእጅቲሃድ (የግል ጥረት) የሚገባባት ጉዳይ እንዳልሆነ የጠነከረ ንግግራቸው ያመለክታል፡፡ ለምሳሌ፡- አመፀኛ ፣ የተረገመ፣ ሰይጣን፣ የሙዚቃ መሳሪያውን በሰዎቹ ጭንቅላት ላይ ሰብረው ፣ ገቢያቸው የከፋና የመሳሰሉትን ጠንካራ ቃላት ባልተጠቀሙ ነበር፡፡

ለ. ከእነርሱም መሐል የፈቀደ መኖሩ ፍፁም አልተዘገበም።

ሐ. የአራቱ መዝሃብ መሪዎችንም ንግግር እንዳስተዋልነው በጥንካሬ ነው ያወገዙት፡፡ ከወንጀል እንደቆጠሩት፣ የምስክርነትቃሉን ውድቅ ከሚያደርግበትና ክብሩን

ከሚያጐድፍ ወንጀልና ተግባሪውንም ቅናት የሌለው ግዴለሽ ፣ቂል ብለው መመደባቸው። በግልፅ የሚያሳየው በአንድነት ያለምንም ተቃርኖ ሐራም መሆኑን ነው፡፡ የተወዛገቡበት ጉዳይ ቢሆን ኖሮ አስተያየታቸውን ሰጥተው ያልፉሉ እንጂ ይህን ያህል አያጠብቁም ነበር፡፡ ከፍትሃዊነታቸው የተነሳ እኛ ዘንድ እንዲህ ነው ስህተትም ሊሆን ይመቻል ይሉ ነበር ። ምክንያቱንም ይህን ያህል ካወሳን ሰለፎች (ቀደምቶቹ) ዘንድ በአንድ ድምፅ፣ በስምምነት ያለምንም ቅራኔ እና ተቃወሞ ሐራምነቱ የፀደቀ መሆኑን ከገለፁ ታላለቅና ስመጥር የኢስላም መሪዎች እና ሊቆች ጥቂቶችን ከነ መዝሃባቸው እንጠቅሳለን ፡፡



1. አቡ ዑመር ኢብኑ አብዱልበር (ማሊኪይ)
2. አቡ ዑመር ኢብኑ አስላህ (ሻፊዒይ)
3.አቡ አጠይብ አጠበሪ
4.አቡ ዐብደላህ ኢብኑ በጣ አልዑክበሪ
5.ሸይኸል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያህ (ሀንበሊይ)
6. አቡበክር መሐመድ ኢብኑ አልሁሰይን አልአጁሪ
7.አቡልፈረጅ ኢብኑ ረጀብ
8.አቡያህያ አሳጂ
9.አቡዘከሪያ አነወዊ (ሻፊዒይ)
10.አቡል ቃሲም አራፊዒ
11.ሙወፊቅ አዲን ኢብኑ ቀዳማህ
12.ዒማዱዲን ኢብኑ ከሲር
13.አህመድ ኢብኑ ሀጀር አልሀይተሚ
14.ሳሊም ኢብኑ አዩብ አራዚ
15.ሺሃቡዲን አልአዝሩዒ
16.አቡበክር ኢብኑል ሙንዚር አነይሳቡሪ
17.ቡርሃኑዲን ኢብኑ አብዱልሐቅ (ሐነፊይ)
18.አቡል ወሊድ ኢብኑ ሩሽድ አልቁርጡቢ
19.ጀማሉዲን አልበርዚ
20.ዐብዱላህኢብኑአቢዐስሮን
21.መሐመድ ኢብኑ አህመድ አልቁርጡቢ (ማሊኪይ)
22.አቡጃዕፈር ኢብኑ ጀሪር አጠበሪ
23.ሸምሱዲን ኢብኑል ቀይም አልጀውዚያህ
24.አቡኢስሃቅ አሽይራዚ
25.ሸምሱዲን አልጀውጀሪይ
26.ሸረፈዲን ኢብኑ ቁዳማህ

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት 26 ታላላቅና ታዋቂ ዓሊሞች (ሊቆች) የዘፈንን ሐራምነት በአንድ ድምፅ ሁሉም የተስማማበት ጉዳይ መሆኑን በየኪታቦቻቸው እናገኛለን፡፡ ታላቁ ዓሊም ኢብኑ ሀጀር አልሀይተሚ ይህንን የጋራ ስምምነት በማስመልከት “ከዚህ ተቃራኒ የዘገበ በእርግጥም የተሳሳተ ወይም ስሜቱ እስኪያውረው ፣ እስኪያደነቁረውና ከቅኑ መመሪያ እስኪከለክለው ድረስ አሸንፎታል፡፡ ከሱናውና ከተቅዋ (አላህን ከመፍራት) አንሸራቶታል” ብለዋል።

አላህ መልካሙን እና እውነተኛውን መንገድ ይምራን ፣ በእዚያውም ላይ እስከመጨረሻው ያጽናን ።

موقع المكتب على
خرائط Google

الحساب العام
SA 21 8000 0251 6080 1007 5881

حساب الوقف
SA13 8000 0251 6080 1017 7778

+966 11 488 4496
+966 11 482 7489
+966 55 4455 643
info@yaqeenweb.com
yaqeenweb
www.yaqeenweb.com